የሰበር መ/ቁ. 18199

ህዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች:- ዶ/ር ምናሴ እሸቱ

ተጠሪዎች:- እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች)

በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈፅም የቀረ ገዢ ባጋጠመ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ሥርዓት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429

የአሁኑ አመልካች ፍርድ በማስፈፀም ላይ የነበረ ፍርድ ቤት ባወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት የገዛ፣ ቢሆንም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በዚህ መሠረት የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ይከፈል በማለት ትዕዛዝ ሊሰጥ በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ:-

**ውሣኔ** :-የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል::

1. በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚቻል በሕግ አልተመለከተም::
2. የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል::

የሰበር መ/ቁ. 18199

ህዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዶ/ር ምናሴ እሸቱ ጠበቃ አፀደወይን ተክሌ ቀረቡ::

ተጠሪዎች፡- እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች) - የ1ኛ ተጠሪ ወኪል ቀረቡ::

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል::

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በቀረበው የሰበር አቤቱታ የተነሣው የሕግ ጥያቄ በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረ ገ[illegible] ባጋጠመ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ሥርዓት የሚመለከት ነው:: አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማፅናት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ 192/97 ታህሣሥ 7 ቀን 97 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው::

ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች ፍርዱን በማስፈፀም ላይ በነበረው ፍ/ቤት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት (ሆስፒታል) ገዝቶአል:: ሆኖም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም:: የሰጠው ምክንያትም ንብረቱን ተረከብ የተባልኩት ስወዳደር ካሰብኩት እና በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ከተመለከተው ውጪ ነው
የሚል ነው:: የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ (ተቃውሞ) አልተቀበለም:: ይልቁንም አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሉ

በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ይከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቶአል:: በዚህ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትምትክክል ነው ብሎአል::

እንደምናየው ጉዳዩ በፍትሐብሔር ረገድ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው:: ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ - ሥርዓት ሕጉ በሰባተኛው መጽሐፍ ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጦአል:: በፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥነ - ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ደግሞ ከቁ.422 እስከ 431 በተለይ ተቀምጠዋል:: ከእነዚህም ውስጥ አሁን ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁ.429 ነው:: ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው ገገርው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ ነው:: በእርግጥ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛውና ዋጋውን ያልከፈለው ተጫራች ልዩነቱንና ኪሣራውን እንዲከፍል እንደሚገደድም ድንጋጌው ያመለክታል:: ከዚህ ውጪ ግን በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚችል በሕጉ አልተመለከተም:: ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት በጥብቅ መከተል ያለበትም ሕጉን ብቻ ነው:: በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉ ከሚለው ውጪ አመልካች የጨረታውን ዋጋ እንዲከፍል እና ንብረቱንም በግድ እንዲረከብ ነው የታዘዘው:: ስለዚህም ትእዛዙ (አቤቱታ የቀረበበት) መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል::

**ው ሣ ኔ !**

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 192/97 የሰጠው ትእዛዝ እና በዚህ ትእዛዝ ፀንቶ የነበረው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል::
2. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው በየራሳቸው ይቻሉ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::